# የቅንጅት ደጋፊዎች መድረክ በአትላንታ

## የወቅቱን በሰሜን አሜሪካ የቅንጅት ድጋፍ ኮሚቴ ውስጥ የተፈጠረውን አለመግባባት አስመልክቶ የደረስንበት የመግባቢያ ሰነድ

በግንቦት 1997 የኢትዮጵያ ህዝብ ለነፃነቱና ለዲሞክራሲ ያለውን ቁርጠኝነት አለምን ባስደነቀ ሁኔታ አሳይቶአል;; በዚህም ጨዋና የሰለጠነ ህዝብ መሆኑን አስመስክሮአል;; ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ይህ የህዝብ የነፃነትና የዲሞክራሲ ጥማት የወለደው ፓርቲ ነው;; ይህ ፓርቲ በግንቦት 1997 ምርጫ ህዝቡን የድል ባለቤት ለማድረግ ህዝባዊ ትግሉን ያቀጣጠለና የመራ ነው;; እንደሚታወቀው የቅንጅት ለአንድነትና ዲሞክራሲ ትግል በአገር ቤት በርካታ አደገኛ ጋሬጣዎች ሲገጠሙት እንደነበር የትላንት ትውስታችን ነው;; በመሪዎቹ ፤ በአባላቱና በደጋፊዎቹ ላይ ወያኔ ያደርስ ከነበረው ማዋከብ ፤ አፈናና ግድያ በተጨማሪ በውስጥ በእነ ልደቱና በጓደኞቹ የተፈፀመበት ክህደት ልባችንን ምን ያህል እንዳደማው የህዝብ ወገኖች የሆንን ሁሉ በቁጭት የምናስታውሰው ነው;;

ከዚህ ሁሉ በሁዋላ ወያኔ የቅንጅት መሪዎችን ፤ የነፃውን ፕሬስ ጋዜጠኞችንና የሲቪክ ማህበራት አባላትንና መሪዎችን በማሰርና በመላው አገሪቱ መንግስታዊ ሽብር በመፍጠር የአገር ቤቱን ትግል ለጊዜውም ቢሆን ማፈን ሞክሮአል;; በመሆኑም በመላው አለም የሚገኙ የቅንጅት ድጋፍ ሰጭ ኮሚቴዎች ትግሉን አቅጣጫ በማሳየት የታሰሩት እንዲፈቱና የነፃነትና የዲሞክራሲ ትግሉም ለውጤት እንዲበቃ የበኩላቸውን ያደርጋሉ የሚል ተስፋ ነበረን;;

ይሁንና ይህ ሳይሆን ቀርቶ ዛሬ የቅንጅት የሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ሰጭ ድርጅቶች ኮሚቴ የመሰነጣጠቅ እድል ገጥሞታል;; በዚህም ነፃነታችንን ናፋቂ ኢትዮጵያዊያን በእጅጉ አዝነናል;; ልባችንም ደምቷል;; ሆኖም ኢትዮጵያዊያን በዚህ ተስፋ ቆርጠን እጆቻችንን አጣምረንና የአገራችንና የወገኖቻችንን መከራ ረስተን መቀመጥ አለብን ብለን አናምንም;; በመሆኑም እኛ በአትላንታ የምንገኝ በግል ተነሳሽነት የተሰባሰብን የቅንጅት ደጋፊዎች የተፈጠረውን ሁኔታ በመገምገም የሚከተለውን ሀሳባችንን ይፋ ለማድረግ ፈቅደናል;;

1. የተፈጠረው ልዩነት በህዝቡ የትግል ስሜት ላይ በረዶ ከመቸለስ ባለፈ በየትኛውም ወገን ላሉ የህዝብ ወገኖች እንዳልጠቀመና የማይጠቅምም መሆኑን ገምግመናል;;

2. ይልቁንም ብቸኛ ተጠቃሚዎች ወያኔና የወያኔ ተላላኪዎች መሆናቸውን ተገን ዝበናል;;

3. የአትላንታ የቅንጅት ድጋፍ ቻፕተር ተጠሪዎች በተፈጠረው ቀውስ ዙሪያ የወከላቸውን (እንወክለዋለን የሚሉትን) በአትላንታ የቅንጅት ደጋፊዎችን ሳያነጋግሩ አንዱን ወገን በመደገፍና ሌላኛውን በማውገዝ የወሰዱትን አቋም ተገቢ ነው ብለን አናምንም;; ምክንያቱም የውክልና ዲሞክራሲ ማለት የተወከለ አካል በማናቸውም ጉዳይ ላይ የወከለውን አካል ተክቶ ይወስናል ማለት አይደለም;; በእንዲህ ባሉ ወሳኝ ክስተቶች ላይ ጉዳዩን ለወከለው አካል አውርዶ ለውይይት ማቅረብ ይገባ ነበር እንላለን;;

4. አሁንም ቢሆን በሁለቱም ወገኖች የታመነ እና የተሰየመ ሶስተኛ ወገን ጣልቃ ገብቶ ችግሮቻቸውን በውይይት እንዲፈቱ ሁለቱም ወገኖች ፈቃደኝነታቸውን እነዲያሳዩ ወገናዊ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን;;

5. በኛ በኩል በአትላንታ የሚገኙ የቅንጅት ደጋፊዎችና ሌሎችም አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን በቀውሱ ዙሪያ በቂ መረጃ እንዲያገኙ እና በችግሩ አፈታትም ላይ

የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማድረግ እንዲችሉ ሁለቱንም ወገኖች (በተለያየ ጊዜ) ለመጋበዝ በዝግጅት ላይ እንገኛለን;; በዚህ በኩል ፈቃደኝነቱ ካለ ከአትላንታ የቅን ጅት ድጋፍ ኮሚቴ ጋር ለመነጋገርና በጋራ ለመስራት ዝግጁ መሆናችንን እንገልጻለን;;

በመጨረሻም በመላው አለም ለሚገኙ የቅንጅት ደጋፊዎችና አገር ወዳድ ኢትዩድያውያን የምናስተላልፈው መልእክት ፣የተፈጠረው ሁኔታ የሚያሳዝንና የሚያስቆጨን ቢሆንም በዚህ ምክንያት ተስፋ ቆርጫለሁና ስለአገሬና ስለወገኔ አላይም ፤ አልሰማም ማለት ለግል ድክመታችን ምክንያት መፈለግ ይሆናል;; በትግል ውስጥ ውጣ ውረድ መኖሩን ተገንዝበን የተፈጠሩ ችግሮችን መነሻና አካሄድ እን መርምር ፤ በትግሉም ውስጥ ተሳትፏችንን እንቀጥል;;

ትግላችንን እግዚአብሄር ይባርክ!

**አድራሻችን ፤** groupatlanta@gmail.com